# “ፈረንጅ አምላኩ…” ማን ነው? ፯ኛ

ገ/ኢ. ጐርፉ

**ሌላው ዓብይ ችግር ሆኖ ሳይፈታ በይደር ተቀምጦ ያለው የሃገር እክል ከኤርትራ ጋር ባለው የጠረፍ ጉዳይ ነው። በዚያም ላይ ግልጽ የሆነ የፈረንጅ አምልኮ ሁኔታ ታይቷል። ጠረፉን ተወልደው ያደጉበት፣ ከየትኛው ኮረብታ ተነስቶ እስከ የትኛው ግራር፣ ከየትኛው ወንዝ ዳርቻና መሸጋገሪያ እስከ የትኛው ቆጥና ዲንጋይ መሆኑን ቆጥረው፣ አበጥረው፣ አንጠርጥረው የሚያውቁ የድንበሩ ተወላጆች መኖራቸው አይሳትም። ይህ እንደ ማንኛውም የሃገር ድንበር እንጂ ልዩ የሚያርገው ነገር የለውም።**

**እንግድያው የድንበሩ ተወላጆች፣ በዕድሜ የበሰሉ አሮጊቶችና ሽማግሎች ስለ ድንበሩ ተጠይቀዋል ወይ? መጠየቅም ሆነ ለጠበቆችና ለሕግ ሰዎች ቃላቸውን የሰጡበት፣ ያማከሩበትም ጊዜ የለም። ይህ ብቻም አይደለም፤ ኢትዮጵያ ወደ ዓለም ሸንጐ፣ በሄግ ፍርድ-ቤት ወክለዋት የቀረቡ ሰዎች እነማን ናቸው ብለን ስንጠይቅ የሚከተለውን የስም ዝርዝር እናገኛለን፦**

**The Federal Democratic Republic of Ethiopia, represented by*:**
**Counsel and Consultants**

**1.** Mr. W. DeVier Pierson, Piper Rudnick LLP, Washington, D.C.; Member of the Bar of the District of Columbia; Member of the Bar of the Supreme Court of the USA.
**2.** Professor Sean D. Murphy, George Washington University Law School, Washington, D.C. Member of the State Bar of Maryland
**3.** Mr. Don C. Lewis, Piper Rudnick LLP, Washington, D.C.; Member of the Bar of the District of Columbia; Member of the State Bar of Texas
**4.** Mr. Edward B. Rowe, Piper Rudnick LLP, Washington, D.C.; Member of the Bar of the District of Columbia; Member of the State Bar of Colorado
**5.** Ms. Virginia C. Dailey, Piper Rudnick LLP, Washington, D.C.; Member of the Bar of the District of Columbia; Member of the Law Society of England & Wales; Member of the State Bar of Florida
**6.** Mr. Thomas R. Snider, Piper Rudnick LLP, Washington, D.C.; Member of the Bar of the District of Columbia; Member of the State Bar of Massachusetts
**7.** Mr. Won Kidane, Piper Rudnick LLP, Washington, D.C.; Member of the Bar of the District of Columbia; Member of the State Bar of Illinois
**8.** Ms. Christina Evans, Piper Rudnick LLP, Washington, D.C.; Consultant

**ከነዚህም የበላይ ሓላፊ በመሆን የተሳተፉ በኔዘርላንድ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሦስት ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች ሲኖሩ፣ ሌሎቹ ግን ከሚስተር ዎን ኪዳኔ በቀር ሰባቱም የውጭ ደሞዝተኞችና ለገንዘብ ጥቅም ብቻ የቆሙ ነበሩ። ይህም ማለት ኢትዮጵያ ረታችም፣ ተረታችም ከፍያቸው በምንም የማይቀርባቸው የውጭ ቅጥረኞችን ይዞን ነበር ከዓለም ሸንጎ የቆምነው ማለት ነው። ታድያ፣ ችሎታ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ጠበቆች የሉም? መልሱ፤ የፈረንጅ አምልኮ ሆነ እንጂ፣ ሰው መች ጠፋ? ብዙዎች ነበሩ!**

**ይቀጥላል…**

* Source:- http://www.pca-cpa.org/upload/files/Eritrea%20Central%20Front%20award.pdf